# የዜጎች መድረክ

ኢዜማ

ቅፅ 1 ቁጥር 14 ጥቅምት 7 ቀን 2012 ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ


# ጤና እና የጤና አጠባበቅ በኢትዮጵያ፤ የኢዜማ ፖሊሲ አቅጣጫ



# አዕኑዖት

## «የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት» አለማክበር ጉዳቱ የሁላችንም ነው !

«የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነት እና አቤቱታ የማቅረብ መብት» በግንባር ቀደም ከሚጠቀሱ ዓለምአቀፍ እውቅና ከተሰጣቸው ሰብዓዊ መብቶች መሀል ናቸው። የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥትም ለዚህ መብት በአንቀጽ 30 ሰፊ ቦታ ሰጥቶ ሙሉ እውቅና እና ጥበቃ ችሮታል።

ይሁን እንጂ እንደብዙዎቹ መብቶች ሁሉ ይህ መሠረታዊ የሆነ ሰብዓዊ መብትም በኢሕአዴግ የአገዛዝ ዘመን በአዋጅ ከመደንገጉ ውጪ በሥራ ላይ ሲውል አልታየም። ባለፉት 28 የኢሕአዴግ የአገዛዝ ዘመናት ይህንን መብት በሥራ ላይ ባለማዋሉ ዜጎች ከመንግሥት እውቅና ውጪ ድምፃቸውን ለማሰማት ተገደዋል፤ ድምፃቸው የሚሰማቸው ባጡ ጊዜም የተጣባቸውን እገዳዎች በመጣስ ሕዝባዊ እምቢተኝነትን ተግባራዊ አድርገዋል።

ለማስታወስ ያህል፤ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ይህ መብት በመነፈጋቸው ለዓመታት የዘለቀ «የድምፃችን ይሰማ» ንቅናቄ በሚያስደንቅ አደረጃጀት መርተዋል፤ በዚህ ትግል የሕይወት ዋጋ ከፍለዋል፤ ተደብድበዋል፤ ታስረዋል፤ ተሰደዋል። በተመሳሳይ ኢትዮጵያዊያን ወጣቶች በሰላማዊ መንገድ አቤቱታዎችን አቅርበው ሰሚ በማጣታቸው ወደ ተደራጀ ሕዝባዊ እምቢተኝነት በመግባት ሥርዓቱን ታግለዋል፤ በዚህ ሂደትም ከፍተኛ የሕይወት መስዋትነት ከፍለዋል፤ አስከፊ ሰቆቃዎች ተፈጽሞባቸዋል። ይህም ሆኖ ትግላቸው ሥርዓቱ ራሱን እንዲፈትሽ አስገድዷል። አሁን ያለው የለውጥ አመራርም የዚህ ትግል ድምር ውጤት እንደሆነ የሚገነዘብ መሆኑ ደጋግሞ ገልጿል።

በዚህም ምክንያት በሰላማዊ መንገድ «ድምፄ ይሰማ» የሚል ወገንን ማፈን የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር አመጽ እንደሚጠራ፤ አመጽ ከተነሳ ደግሞ በቀላሉ እንደማይበርድ ይህ አመራር ከሌሎቹ በተሻለ የማወቅ እድል አለው።

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ማንኛውም የኅብረተሰብ ክፍል በመንግሥት ላይ ያለውን ተቃውሞም ሆነ አቤቱታ በሰላማዊ መንገድ የማቅረብ መብቱ ሊረጋገጥ ይገባል፤ መንግሥት ለዚህ መብት እውቅና ብቻ ሳይሆን ጥበቃ ማድረግ ይኖርበታል ብሎ ያምናል።

ኢዜማ፣ አሁን በስልጣን ላይ ያለው አመራር ይህን መብት በማስከበር ረገድ ማድረግ የሚገባውን አላደረገም ብሎ ያምናል፤ ለዚህም የሚከተሉትን ማስረጃዎች መጥቀስ ይቻላል።

1. በብዙ ክልሎች ተቃውሞን በተደራጀ መንገድ በአደባባይ ማቅረብ ቀርቶ በአዳራሾች ውስጥ እንኳ መነጋገር የማይቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል። የድጋፍ ካልሆነ በስተቀር የተቃውሞ ወይም የአቤቱታ ሰልፎች ብቻ ሳይሆን የአዳራሽ ውስጥ ስብሰባዎችም በብዙ የሀገራችን አካባቢዎች የማይታሰቡ ሆነዋል።
2. በክልሎችም ብቻ ሳይሆን በአዲስ አበባ ከተማም ይህን መብት ማስከበር አልተቻለም። በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ላይ ጥያቄ ያላቸው ወገኖችም ተሰባስበው ጥያቄያቸውን በሰላማዊ መንገድ ማቅረብ አልቻሉም።

ኢዜማ «የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት» መከበር አለበት ብሎ ያምናል። ይህ መብት በሕገ መንግሥት መፃፉ ብቻውን ለኢዜማም ሆነ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚሰጠው ፋይዳ የለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገው ይህ መብት ተግባራዊ ሆኖ ማየትን ነው፤ የኢዜማም ፍላጎት ይኸው ነው።

«የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት» የማስጠበቅ ተቀዳሚ ኃላፊነት የመንግሥት ሆኖ እያለ በመንግሥት አካላት መጣስ መቀጠሉ አሳዛኝ ነው፤ አስቸኳይ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል። መሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ እና አቤቱታ ማቅረብ ከደህንነት ጋር በተያያዘ ወይንም በሌላ ምክንያት ለጊዜው ማድረግ የማይቻል ሆኖ በተገኘ ጊዜም መንግሥት ያለውን አደጋ ወይንም ምክንያት ለዜጎች በግልጽ አስረድቶ አማራጭ ጊዜ ወይም ቦታ የመጠቆም ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል፡፡

ኢዜማ «የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግና ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት» ተግባራዊ አለማድረግ ጉዳቱ የሁላችንም መሆኑን ማስታወስ ይወዳል።

# በሰሜን አሜሪካ በተለያዩ ከተሞች የዓለምአቀፍ ድጋፍ ማሕበር ምርጫዎች እየተካሄዱ ነው

ጥቅምት 06 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማሕበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ዓለምአቀፍ ድጋፍ ማኀበር በአሜሪካ እና በካናዳ ምርጫ ማካሄዱን የኢዜማ ዓለምአቀፍ አባላት ተጠሪ ኢዮብ መሳፍንት ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡

በሀገረ አሜሪካ ከዋሽንግተን ዲሲ ቀጥሎ በተካሄደው ምርጫ አትላንታ እና ሲያትል ከተሞች አመራሮቻቸውን መርጠዋል፡፡ በአትላንታ ከተማ በተካሄደው ምርጫ ፋንታሁን ሹሜ፣ ውብሸት ንጋቱ፣ ፍቅረዓለም ሙላቱ፣ ፋሲል ጋሹ እና ምትኩ ተሾመ ለከተማ ኮሚቴ አመራርነት የተመረጡ ሲሆን ለክፍለ ዓለማትና ዓለምአቀፍ ኮሚቴዎች አመራርነት ሹሜ ጅሩ፣ ምንተስኖት ሀይለማሪያምና አያሌው ተሊላ (ዶ/ር) ተመርጠዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በሲያትል ከተማ በተካሄደው ምርጫ ነጋ አባተ፣ ሰይፈ ኃ/ሚካኤል፣ ፈቃዱ ተሰማ፣ እንዳለ አንዲኖ እና ቢኒያም ደሜ ለከተማ ኮሚቴ አመራርነት ሲመረጡ መቅደላ ተለለ እና ሰለሞን ተስፋዬ ለክፍለ ዓለማትና ዓለምአቀፍ ኮሚቴ አመራርነት ተመርጠዋል፡፡ በሀገረ ካናዳ በቶሮንቶ ከተማ በተካሄደው ምርጫም ኒቆዲሞስ ሮማን፣ ሀብታሙ መኮንን፣ ፋኖስ ደበበ፣ ቦሩ ዱብሊበን እና ፍቃዱ ደስታ ለከተማ አመራርነት የተመረጡ ሲሆን ፍስሐ ያዕቆብ፣ ጆኒ ብርሃኑ እና ፋሲል አስማሬ ለክፍለ ዓለማትና ዓለምአቀፍ ኮሚቴዎች እንደተመረጡ ለዜጎች መድረክ የደረሰው መረጃ ያስረዳል፡፡

ቀጣይነት ባለው መልኩ የዓለምአቀፍ ድጋፍ ማኀበር ምርጫዎች በተለያዩ ከተሞች እንደሚካሄድ ለማወቅ ተችሏል፡፡


## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኀበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

ጥቅምት 7 ቀን 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ጤና እና የጤና አጠባበቅ በኢትዮጵያ፤ የኢዜማ ፖሊሲ አቀጣጫ

## መግቢያ

የማኅበራዊ ፍትህ እሳቤ የአንድ ሀገር አስተዳደራዊ መዋቅር በማኅበረሰብ ውስጥ ሚዛናዊና ፍትሃዊ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፤ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ግንኙነትንና ትስስርን ለማስረፅ የሚጠቀሙበት ማኅበራዊ አስተሳሰብ ነው::

በማኅበራዊ ፍትህ አስተሳሰብ መሰረት በማኅበረሰብ ውስጥ ሚዛናዊ ፍትህ ለመስፈኑ ጠቋሚና አመላካች በመሆን የሚያገለግሉት መለኪያዎች በማኅበረሰቡ ውስጥ የሰብዓዊ መብቶችን ማለትም በሕይወት መኖር፣ የሃሳብና ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ ፍትሃዊ የሆነ የሃብት ክፍፍልና ተጠቃሚነት ሲረጋገጥ፤ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮችና ክንውኖች ውስጥ ሰዎች ከአድሎ የነፃና ቀጥተኛ ተሳትፎ ሲኖራቸው፤ በማኅበረሰባቸው ውስጥ በሚኖራቸው ቦታ ምክንያት በሰዎች መካከል የሚፈጠረውን የፖለቲካ ማኅበረሰባዊና ምጣኔ ሀብታዊ ልዩነቶችን በሕዝብ የተመረጠ መንግሥት በሚኖረው የማስተባበርና ፍትህ የማስፍን ሚና ማስተካከል ሲችል ነው::

ፍትሃዊ መሆን ሲባል ዜጎች በማኅበረሰባቸው ውስጥ በሚኖረው የሃብት ክፍፍል ሂደት እያንዳንዱ ዜጋ ባልፈለገውና ባልመረጠው ሁኔታ በማኅበረሰቡ ውስጥ በሚኖረው ቦታ (Status) ምክንያት ተጠቃሚ ለማይሆኑ፣ ለሚገለሉና ነፃነታቸውን በአግባቡ ለመጠቀም ለማይችሉ የማኅበረሰቡ አባላት በማኅበረሰብ ማካካሻ ድጋፎች አማካይነት በሃብታም እና ደሃ፣ በወንድ እና ሴት፣ በገጠር እና ከተማ ነዋሪዎች፣ በአርሶ አደርና እና አርብቶ አደር መካከል የኑሮ ደረጃ ልዩነታቸው እንዲጠብ በማስቻል ላይ የተመሠረተ ነው:: በዚህ አስተሳሰብ በሚመሩ ሀገሮች ውስጥ የሚፈጠረውን ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሃብታዊ፣ ልማዶችና የደንቦች ሚዛን መዛባትን ለማስተካከል ጥረት የሚደረገው በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠረውን የሀብት ልዩነት ለማኅበረሰቡ አባላት በሙሉ በጋራ ተጠቃሚ ለማድረግ በሚደረግ ጥረት ነው::

### ፍትሃዊ ጤና እና የጤና አገልግሎቶች

በማኅበራዊ ፍትህ አስተሳሰብ የሚመሩ መንግሥታት የማካካሻ ድጋፎችን በተጠናከረ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግና የጤና አገልግሎቱን ፍትሃዊ ለማድረግ የግብር ሥርዓቱን መልክ ማስያዝ፣ ዘመናዊ በማድረግና ውጤታማ ማድረግን፤ የመንግሥት፣ የግል ተቋማት እና የማኅበረሰቡን ትብብርና መቀናጀት ማጠናከር፤ የማኅበረሰብ የጤና ዋስትና መመስረትና ከጤና ኢንሹራንስ ሰጪዎች ጋር ማስተሳሰር፤ ፍትሃዊ ተደራሽነት ያለው የጤና፣ ጤና አገልግሎት (ማኅበረሰባዊ ጤና/ public health፣ ፈውስ ሰጪ (Curative) ጤና አገልግሎቶችና መድኃኒት አቅርቦት) ማረጋገጥ፤ አሠሪና ሠራተኛ ሕጎችን የሠራተኛውን ደህንነት በሚያስጠብቅ መልኩ ተግባራዊ ማድረግ እና በጤናው ዘርፍም ሆነ በሌሎች የገበያ ቁጥጥር ሥርዓቶችንና ተቋዋማትን መመስረት፣ ማጎልበትና ማሳደግ ተቀዳሚ ተግባር ይሆናል::

ከላይ ከተጠቀሱት የማኅበራዊ ፍትህ እሳቤዎች በተጨማሪ አንድ መቶ ስልሳ ሀገሮች የፈረሙበት ዓለም አቀፋዊ የኢኮኖሚ፤ ማኅበራዊ እና ባህላዊ መብቶች ስምምነቶች ተግባራዊነታቸውን ያረጋግጣሉ:: የማኅበራዊ ዋስትና፤ የተስተካከለ የቤተሰብ ሕይወት፤ የመማርና በባህላዊ ሁነቶች ውስጥ በቀጥታ የመሳተፍ መብቶች ዋና ዋናዎቹ የስምምነቱ አካሎች ናቸው:: በአጠቃላይ ስምምነቱ ባንድ ማኅበረሰባዊ ሥርዓት ውስጥ በከፍተኛ ጥራት ላይ የተመሠረተ፤ ተደራሽነትና ፍትሃዊነትን ዓላማው ያደረገ የአካላዊና አእምሮአዊ ጤናን በማረጋገጥ የተረጋጋ፣ ጤናማና አምራች ማኅበረሰብ ለመፍጠር ከሚያስፈልጉ ሁነቶች ውስጥ ዋናዋናዎቹ መሆናቸውን ያረጋግጣል:: በተለያዩ ሀገራት የሚገኙ ተመራማሪዎች መፍትሄ አመላካች የሆኑ የጥናትና ምርምር ውጤቶቻቸው እንደሚያሳዩት፣ በሥነ - ምግባር በእውቀትና በክህሎት የታነፀ የሰው ሃብት፣ በቂ ምግብ ማምረትና አማራጭ ምግቦችን ማብዛት፣ ንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ ውጤታማና ወቅታዊ የሆነ የፈውስ ህክምና አገልግሎት መስጠት፣ በሽታን በመከላከል ላይ ያተኮረ ክንውን፣ የግልና የመኖሪያ አካባቢ ንፅህናን መጠበቅ የአንድን ማኅበረሰብ ጤንነትን ከሚወስኑት ዋና ዋና ምክንያቶች ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው::

ከላይ ከተጠቀሱት የማኅበረሰብን ጤና ከሚወስኑ ኹነቶች በተጨማሪ ሰዎች በማኅበረሰባቸው ውስጥ በሚኖራቸው ቦታ (status) ምክንያት በሃብታምና ድሃ፣ በወንዶችና ሴቶች፣ በከተማና ገጠር፣ በተማሩና ባልተማሩ፣ በአራሽ ገብሬና ከብት አርቢ መካከል የሚፈጠሩ ልዩነቶች በማኅበረሰብ ጤና ላይ ተጨማሪ ተፅዕኖ ይፈጠራሉ:: ከላይ የተዘረዘሩት ለማኅበረሰብ ጤና መታወክ ምክንያቶች ተደርገው የተዘረዘሩት ሁኔታዎች የሚያመላክቱት የማኅበረሰብን ጤና ለማስጠበቅ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች ከተለያዩ አቅጣጫዎችና ዘርፈ ብዙ የሆኑ አካላት ጋር በጋራ ጥረት መደረግ እንዳለበት ያመላክታሉ:: በዚህም መሠረት የጤና እና ጤና አገልግሎት አሰጣጡ በተመራማሪዎች፣ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ የጤና ዋስትና አገልግሎት ሰጪዎች፣ መንግሥታዊ ድርጅቶች (ጤና፣ ግብርና፣ ትምህርት፣ ውሃ ሚኒስቴሮች)፣ የጤና ባለሙያዎችና የሙያ ማኅበራቸው፣ የንግዱ ማኅበረሰብ፣ የማኅበረሰቡ አባላትና ቡድኖች በሚፈጠር የጤና አስተዳደር መድረክ (Shared Health governance) መሆን

ይኖርበታል፡፡

በሥነ - ምግባር በእውቀትና በክህሎት የታነፀ የሰው ሃብት ለማፍራት በተግባር የታገዘ ሁለንተናዊ እውቀትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ፖሊሲ ያለው የትምህርት ሥርዓት፣ በቂ ምግብ ለማምረትና አማራጭ ምግቦችን ለማብዛት ዘመኑ የደረሰባቸውን ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም በቂና አስፈላጊ የምግብ ምርቶችን ማምረት የሚችል የግብርና ሥርዓት፣ ንጹህና በቂ የመጠጥ ውሃ ለሁሉም ማዳረስ የሚችል ሥርዓት፣ ውጤታማና ወቅታዊ የሆነ የፈውስ ህክምና አገልግሎት መስጠት፣ በሽታን በመከላከል ላይ ያተኮረ ክንውን፣ የግልና የመኖሪያ አካባቢ ንፅህናን መጠበቅና ማስጠበቅ የሚችል የጤና ሥርዓት ማስፈን የግድ ይላል፡፡ በድምሩ የግለሰቦችንም ሆነ የማኅበረሰብን ጤና በበቂ ሁኔታ ማረጋገጥና የጤና አገልግሎቶችን በበቂና ፍትሃዊ በሆነ መልኩ በማኅበረሰቡ ውስጥ ለማስፈን የሚቻለው የትምህርት፣ የግብርና፣ የውሃ፣ የጤና፣ የጤና ዋስትና ሰጭዎች፣ የግል ባለሃብቶችና ሌሎችም በጋራ የጤና አስተዳደር መድረክ በመፍጠርና ይህን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ፖሊሲ በመቅረፅ ወደ ተግባር ሲገባ ነው፡፡

## የጤናው ዘርፍ ስኬቶች እና ክፍተቶች

በሀገራችን ባለፉት ዘመናት በመንግሥት ለተያዙ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ የልማት እንቅስቃሴዎች፤ የሰው ኃይል ካፒታል ለመገንባት የተጀመሩ ጥረቶች አሉ፡፡ በነበረው ሥርዓት የጤና አገልግሎት አተገባበር ውስጥ የአፈጻጸም የስታንዳርድ መለኪያዎች ከሆኑት የተደራሽነት፣ ፍትሃዊነት፣ አግባብነት እና ጥራት አንጻር የነበረውን ተሞክሮ መመልከቱ ተገቢነት አለው፡፡ አሁን እየተተገበረ ያለው የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት በተደራሽነትና በአገልግሎቱ ፍትሃዊ ሥርጭት በአንጻራዊነት በጅምር ደረጃ ጥሩ የሚባል እንቅስቃሴ ይስተዋላል፡፡ በዘርፉ ከሚጠቀሱት መመዘኛ መለኪያዎች መሠረት ባለፉት ዓመታት በርካታ የጤና ተቋማት በገጠሩና በከተማ ዕድሉ ባልደረሰባቸው አካባቢዎች በመገንባት ለህፃናት፤ ለእናቶች፤ ለወጣቶችና ለኅብረተሰቡ በአጠቃላይ የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ወይም ለማዳረስ ጥረት ተደርጓል፡፡

እንደ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የ2010 ዓ.ም የሥራ ዘመን ጤና እና ጤና ነክ መረጃዎች ሪፖርት መሠረት አንድ ጤና ኬላ ለ5,516 ሰዎች፤ አንድ ጤና ጣቢያ ለ2,088 ሰዎችና አንድ ሆስፒታል ለ226,096 ሰዎች የጤና አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ የጤና ድርጅቶችን ስርጭትን በተመለከተ አንድ ጤና ጣቢያ ጋምቤላ ውስጥ ለ14,627 ሰዎች፤ አዲስ አበባ ውስጥ ለ36,244 ሰዎችና በሀገሪቱ በአጠቃላይ ለ24,260 ሰዎች የጤና አገልግሎት ይሰጣል፡፡ አንድ ሆስፒታል ጋምቤላ ውስጥ ለ113,361 ሰዎች፤ ኦሮሚያ ውስጥ ለ1,112,529 ሰዎችና በሀገሪቱ በአጠቃላይ ለ389,534 ሰዎች ይሰጣሉ፡፡ ከላይ የተመለከቱት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የጤና ድርጅቶቹ በአጠቃላይ እንዲሁም ከሞላ ጎደል የጤና ድርጅቶቹን ስርጭት የሚከተሉት የጤና አግልግሎቶቹ ስርጭት አሁን ባለው ማንነትን መሠረት በማድረግ በተካለሉት ክልሎች ውስጥ ያለው ስርጭት ፍትሃዊነቱ አጠያያቂ ነው፡፡

በኢትዮጵያ 10% የሚሆኑ ህፃናት በከፋ የምግብ እጥረት ውስጥ ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም 24% የሚሆኑት ከእድሜያቸው በታች ዝቅተኛ የክብደት ደረጃ ላይ ናቸው ፡፡ በኢትዮጵያ እድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት የምግብ እጥረት ሁኔታ አሁንም ከፍተኛ ቢሆንም መሻሻል ታይቶበታል፡፡ (እ.ኤ.አ በ2000 ከነበረበት 57% በላይ እ.ኤ.አ 2016 ወደ 38% ዝቅ ብሏል)፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ከተካተቱት ሴቶች ውስጥ 10% የሚሆኑት የጤና አገልግሎት ለማግኘት ቢያንስ አንድ ተግዳሮት ይጠቅሳሉ፡፡ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ህክምና ፈላጊዎች ለህክምና የሚሆን ገንዘብ ችግር እንዳለባቸው ይጠቅሳሉ፡፡ ግማሽ የሚሆኑት ደግሞ የጤና አገልግሎት መስጫውን ርቀት እንደ ችግር ይጠቅሳሉ፡፡ እንዲሁም በጤናው ዘርፍ የአመራር እና አደረጃጀት ጤና ላይ ተፅኖ ያላቸው ቤተሰባዊና ኅብረተሰብ አቀፍ ምክንያቶች (እውቀት፣ አመለካከት እና ተግባር) ላይ የሚታዩ ክፍተቶች ሰፊ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ እንደ እ.ኤ.አ በ2016 የተካሄደው የሥነ ሕዝብ (Demograph) ጤና ዳሰሳ ጥናት እንደተመለከተው የህፃናት ሞት መጠን እ.ኤ.አ ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ በከፍተኛ ሁኔታ እየቀነሰ መጥቷል፡፡ እ.ኤ.አ በ2000 ዓ.ም ከነበረበት 97/1000 (ከ1000 ሕፃናት 97 ሞት) እ.ኤ.አ 2016 ላይ 48/1000 (ከ1000 ህፃናት 48 ሞት) ዝቅ ብሏል፡፡ በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት ሞት እ.ኤ.አ 2000 ላይ ከነበረበት 166/1000 እ.ኤ.አ 2016 ላይ ወደ 67/1000 ዝቅ ብሏል፡፡ በመውለድ እድሜ ክልል ያሉ እናቶች ሞት መጠን እንደዚሁ በከፍተኛ ደረጃ ቀንሷል፡፡ እ.ኤ.አ 2000 ላይ ከነበረበት 676/100,000 (ከ100,000 እናቶች 676 ሞት) እ.ኤ.አ በ2016 ወደ 412/100,000 (ከ100,000 እናቶች 412 ሞት) ዝቅ ብሏል፡፡ ምንም እንኳን ከላይ እንደተጠቀሰው የህፃናት እና እናቶች ሞት የቀነሰ ቢመስልም ከዓለም አቀፋዊና ከሰሃራ በታች ካሉ ሀገራት አማካይ ጋር ሲወዳደር ኢትጵያ ገና ብዙ ይቀራታል፡፡ ይህ የሆነው በዋናነት ባለፉት አመታት የኢትዮጵያ መንግሥት በመከላከል ላይ ያተኮረ የጤና አገልግሎት ላይ ብቻ በማተኮር የዘመኑ ሳይንስ የደረሰባቸውን የቴክኖሎጂ ውጤቶችንና ግብአቶች በመጠቀም የበሽታ ምክንያቶችን በማወቅና (Diagnosis) ጥራቱንና ደረጃውን የጠበቀ የፈውስ ህክምና አገልግሎት (Curative Services) ለመስጠት ቸልተኝነት በማሳየቱ መሆኑን ሁኔታዎች ያመላክታሉ፡፡ ከእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ የዘመኑ ሳይንሳዊ የእድገት ደረጃ በሚፈቅደው መሠረት የፈውስ ህክምና አገልግሎቶችን ተግባራዊ ለማድረግ የመንግሥትን፤ የኅብረተሰቡን፤ የግልና የመንግሥት የምጣኔ ሃብት ድርጅቶችንና የግል ባለሃብቶችን ጥረትና ድርሻ በማስተባበርና በማቀናበር የጤና አገልግሎቱን ፍትሃዊና በተመጣጣኝ ዋጋ ተደራሽነቱን ባለማረጋገጡ ነው፡፡

## የኢዜማ የጤና እና የጤና አገልግሎት ፖሊሲ አቅጣጫዎች

በሀገራችን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ተነስተን ወሳኝ የሆኑ የማኅበረሰብ ጤና መስኮች (የእናቶች እና የሕፃናት ጤንነትን በማረጋገጥ ሞትን መቀነስ፣ ወጣቶች ሥነ ተዋልዶ ጤና፣ ኤች አይ ቪ ኤድስ፣ የተመጣጠነ የምግብ አቅርቦት ወዘተ..) እና ዜጎች ደረጃውንና ጥራቱን የጠበቀ የፈውስ ህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣቸዋል፡፡

### በአጭር ጊዜ ፡-

- የመከላከልና ፈውስ ሰጪ ጤና አገልግሎት አቅርቦትና ፍትሃዊነትን ማረጋገጥና ተያያዥነት ያላቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎችን በተሟላ መልኩ ማረጋገጥ፣
- የዘርፉን አመራርና አደረጃጀት

ከፖለቲካ ተፅዕኖ በማላቀቅ ሥራው በሚፈልገው የሰው ኃይል ለማደራጀት ትኩረት መስጠት፡፡

- በሀገሪቱ ውስጥ ያለው ክልል አከላለሉ በመጠኑና በሕዝቦች አሰፋፈሩ ለማኅበራዊ አገልግሎቶች አቅርቦትና ፍትሃዊነት፤ መንግሥት የሕዝብን ሰላምና ደኅንነት ለማስጠበቅ፤ ማኅበረሰቡ እርስ በርስ ያለውን ቅርርብና ትስስር ለማጠናከርና በአጠቃላይ የመንግሥትም ሆነ የማኅበረሰቡ የሥራ እንቅስቃሴዎች የተቀላጠፈና ውጤታማ እንዲሆኑ በሚያስችል መልኩ በራስ አስተዳደር (ፌደራላዊ) ወሰኖች ሲደራጅ የጤና ሴክተሩንም በዚህ አንጻር መቃኘት፡፡
- የጤናው ዘርፍ ሙያ ማኅበራትን በማቀናጀት እና በመደገፍ በባለሙያ ሥነምግባር፤ በህክምና መስጫ ተቋማት ምዘና ብሎም በጥራትና ደረጃ ምደባ ሥራዎች ላይ ኃላፊነት ወስደው እንዲሠሩ ማስቻል፡፡
- ከባህል ህክምና ጋር ተያያዝነት ያላቸው ጥናቶችን በመደገፍ እና በማገዝ ጠቃሚ ከሆኑ ግኝቶች ማኅበረሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ

## በመካከለኛ ጊዜ ፡-

- 
- በሚደራጀው የራስ አስተዳደር ውስጥ ያሉትን የጤና ተቋማት (የማኅበረሰብ ጤና አገልግሎት እና የፈውስ ህክምና ሰጪ ተቋማት) ብዛት፤ ዓይነትና ስርጭት ለይቶ በማውጣት ተደራሽነታቸውንና የስርጭት ፍትሃዊነት ሕዝብን በዕኩልነት በሚያገለግል መልኩ ማስተካከል፡፡
- በዋናነት አንኳር ትኩረት የሚሆነው ጥራቱን የጠበቀ የማኅበረሰብ ጤና አገልግሎት (በወሊድ ጊዜና አዲስ የተወለዱ የጨቅላ ህፃናት እንክብካቤ፤ የተሟላ ክትባት አገልግሎት፤ የተቀናጀ የጨቅላዎችና ህፃናት በሽታዎች መከላከልና ህክምና መስጠት፤ የቤተሰብ ምጣኔ፤ የቅድመ ወሊድ እና ድህረ ወሊድ ክትትል፤ በባለሙያ የታገዘ የወሊድ አገልግሎት . . . ወዘተ ) ለሕዝቡ ማዳረስ ቢሆንም መንግሥት ለተላላፊና ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች የፈውስ ህክምና አገልግሎቱም ተመጣጣኝ የሆነ ትኩረት እንዲሰጠው ማድረግ፡፡
- ቤተሰብ ለአባላቱ ህክምና የሚሆንን ወጪ ለመሸፈን እንዲችል ገቢ ማስገኛ ሥራዎችን እንዲጀምር የሚረዱ ጤና ተኮር ፕሮጀክቶችን ማበረታታትና መደገፍ፤
- አምቺ በሆኑ የራስ አስተዳደር ደረጃዎች የማኅብረሰብ ጤና ዋስትና ማደራጀትና መደገፍ፤
- ኢንሹራንሶች የጤና ዋስትና ፖሊሲያቸውንና መዋቅረቸውን ሀገሪቱ ውስጥ ባለው ነባራዊ ሁኔታ መሠረት እንዲያስተካክሉ እና ተግባራዊ እንዲያደርጉ ማበረታት፤
- በጤና ድርጅቶች፣ በማኅበረሰባዊ የጤና ዋስትናና በኢንሹራንሶች መካከል ግንኙነት መፍጠርና ተደጋጋፊነትንና መቀናጀትን በሚያጎለብት መልኩ ማደራጀት፤
- የማኅበረሰባዊ የጤና ዘርፍ እና የፈውስ ጤና አገልግሎቶችን ከተደራሽነት፤ ፍትሃዊነት እና ከዋጋ ተመጣጣኝነት በተጨማሪ ጥራትና ተቀባይነት ያለው የመከላከልና ውጤታማና ፈዋሽ የህክምና አገልግሎቶችን ለተገልጋዩ ማድረስ፡፡
- በዚህ መሰረት የጤና አገልግሎቱን ጥራትና ተቀባይነት ለመጨመር የሚከተሉት ክንውኖች አስፈላጊ ናቸው፡-
- የጤና ባለሙያዎቹ መሠረታዊና ድህረ - ምረቃ ሥልጠናቸው በአገልግሎቱ የዘመኑ የህክምና ጥበብና ቴክኖሎጂ የደረሰበትን እውቀትና ክህሎት የጨበጡ፣ በግብረ ገብ የታነፁ፣ የሃሳብ ልዕልናቸው ከፍ ያለና ተወዳዳሪ ሆነው እንዲወጡ የጤና ዘርፉን አስተሳሰብና ፖሊሲ፤ የማኅበራዊ ፍትህ አስተሳሰብና ፍልስፍናን መሰረት ባደረገ መልኩ መቅረፅ፡፡
- ለግል ባለሃብቱ ሰብዓዊና ንብረት የማፍራት መብቶችን በማክበር፤ ለንብረቱ ዋስትና በመስጠትና ለሥራ ምቹ ሁኔታን በመፍጠር በፈውስ ጤና አገልግሎት ዘርፍ እንዲሳተፍ ማበረታታትና መደገፍ
- የዘመኑ የእድገት ደረጃ የሚፈቅደውን የህክምና መስጫ መሳሪያዎችንና የአገልግሎት ጊዜያቸውን የጠበቁ ፈዋሽነታቸው የተረጋገጠና ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው መድኃኒቶች በሥራ ላይ እንዲውሉና ለማኅበረሰቡ ጥራቱን የጠበቀና ተቀባይነት ያለው የጤና አገልግሎት ለማዳረስ መሥራት፡፡
- በኢትዮጵያ ለተመደቡበት የሥራ ዘርፍ ብቁ የሆኑ፣ እውቀትና ክህሎታቸው ከፍ ያለ፣ ስብዕናቸውና የአስተሳሰብ ልዕልና ላቅ ያለና ግረገብነትን የታጠቀ የሰው ኃይል፤ ዘመኑ ያፈራቸውን ለሥራው ወሳኝ የሆኑ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን መጠቀም የሚችልና ከሌሎች የገንዘብ ተቋማት፣ ገቢዎች ሚኒስትር፣ የሀገር ደህንነት/ መከላከያ ድርጅቶችና ሌሎችም ጋር በመተባበር የሚሠራ ጤና አገልግሎትና የመድኃኒት ጥራት ተቆጣጣሪና ስርጭት አስተባባሪ ተቋም መገንባት አለበት፡፡
- ኢትዮጵያ ውስጥ ከእውቀት ማነስና ከማኅበረሰባዊ ልማዶች ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ እንዲሁም የምግብ እጥረት በሽታዎችን ለመከላከልና ለማከም የሚያስችሉ ማኅበረሰባዊ ተቋማት እንዲቋቋሙና እንዲጎለብቱ፣ የማህበረሰቡን ቀጥተኛ ተሳታፊነትን ለማጎልበት ማህበረሰባዊ ውይይቶችን ማበረታታትና ከውይይታቸው በመነሳት የመከላከል ሥራ እቅድ አውጥተው ወደ ሥራ እንዲገቡ ድጋፍ ማድረግ፡፡

## የረዥም ጊዜ፡-

ከሌሎች አጋር ዘርፎች ጋር በመተባበር በሀገሪቱ ውስጥ፡-

- በቤተሰብ ደረጃ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በሚደረጉ ጥረቶች ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ፣
- በሰው ልጅና ተፈጥሮ መካከል ያለውን ሚዛን ለማስጠበቅ የተፈጠሮ ይዘቱን እንደጠበቀ ለማቆየትና የተዛባውን ለማሻሻል በሚደረገው ጥረት ንቁ የሆነ ተሳትፎ ማድረግ፡፡
- ከሌሎች ቁርኝት ካላቸው ዘርፎች ጋር በመቀናጀት ዘላቂነት ያለው ጊዜውን መሠረት ያደረጉ ፖሊሲዎችን በመንደፍ የማኅበረሰቡን ጤና በአስተማማኝ መሠረት ላይ ማቆም ነው፡፡

# የኢዜማ የዞን አስተባባሪዎች በጋራ ውይይት አካሄዱ

ጥቅምት 6 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)




የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙ የዞን አስተባባሪዎች ቅዳሜ ጥቅምት 1 ቀን 2012 ዓ.ም በአዲስ አበባ ውይይት አካሄዱ፡፡ በውይይታቸውም ወቅት የዞን አስተባባሪዎች እርስ በእርስ የልምድ ለውውጥ አድርገዋል፤ በሚያስተባብሯቸው የምርጫ ወረዳዎች ያጋጠሟቸውን ተግዳሮቶች በማቅረብ የመፍትሔ አቅጣጫ በጋራ አስቀምጠዋል፡፡
ዘንድሮ በሚካሄደው ሀገራዊ ምርጫ ላይ ማድረግ ስለሚገባው ዋና ዋና ተግባራት፣ ከምርጫው በፊት መሠራት ስላለባቸው ሥራዎች በስፋት ውይይት የተደረገባቸው ሲሆን አጠቃላይ የዞን አስተባባሪዎችም የሥራ ሪፖርት አቅርበዋል፡፡ በሥራ ላይ ያጋጠሟቸውን ከፀጥታ፣ ከማደራጀት ጋር በተያያዘ፣ እንዲሁም በደቡብ ክልል ባለው የኮማንድ ፖስት ምክንያት በነጻነት መንቀሳቀስ አለመቻላቸውን፣ በኦሮሚያ ክልል የወረዳና የዞን አስተዳዳሪዎች በኢዜማ አባላት እና በአመራሩ ላይ የሚፈጥሩት ጫና ቀርበው ኢዜማ ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሠራባቸው ተገልጿል፡፡
በውይይቱ ላይ 25 የሚሆኑ የዞን አስተባባሪዎች ሲገኙ የምስራቅና የምዕራብ ጎጃም፣ የባህር ዳር ዙሪያ፣ የአዊ እና የደቡብ ጎንደር የዞን አስተባባሪዎች ጎሐ ጽዮን ላይ መንገድ በመዘጋቱ ምክንያት በውይይቱ ላይ ሳይገኙ ቀርተዋል፡፡
በኢዜማ መዋቅር ስር ያሉ ዞኖች በስራቸው ከ7 እስከ 22 የሚደርሱ የምርጫ ወረዳዎችን ያስተባብራሉ፡፡

# በኮምቦልቻና በእነዋሪ ሕዝባዊ ስብሰባ ተካሄደ

ጥቅምት 6 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በሰሜን ወሎ ኮምቦልቻና በሰሜን ሸዋ በእነዋሪ ከተማ የኢዜማ አባላት፣ ደጋፊዎችና ኅብረተሰቡ የተሳተፉበት ሕዝባዊ ስብሰባ በተሳካ ሁኔታ ተጠናቀቀ፡፡
በኮምቦልቻ ከተማ የኢዜማ ምክትል ሊቀመንበር ጫኔ ከበደ (ዶ/ር) በእነዋሪ ደግሞ የፓርቲው ዋና ጸሐፊ አበበ አካሉ ተገኝተው ከታዳሚዎች ለቀረበላቸው ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ አስተያየቶችን ተቀብለዋል፡፡ ሕዝባዊ ስብሰባ በተካሄደባቸው በሁለቱም ከተሞች ኢዜማ አዲስ ያመጣው አዲስ አደረጃጀት ላይ ገለጻ ተደርጓል፡፡ ኢዜማ የዜግነት ፖለቲካ እና ማኅበራዊ ፍትህ ብሎ በተነሳባቸው ፅንሰ ሃሳቦች ዙሪያም ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል፡፡
በሁለቱም ከተሞች «እንደ ሀገር አሁን ካለው ችግር እንዴት እንወጣለን? በከተሞች መንገድ መዘጋት ተባብሶ ቀጥሏል፡፡ ይሄን ችግር እንዲቀረፍ ለሚመለከተው አካል አሳውቁልን» የሚሉ እና በእነዋሪ ከተማ በተለየ መልኩ የስኳር እጥረት ማጋጠሙን፣ መንገድ ስለሌለ ምርታቸውን ለገበያ ማቅረብ አለመቻላቸውን፤ ከፍተኛ ችግር ላይ መውደቃቸውን ለእነዚህ ችግሮች መፍትሔ እንዲበጅላቸውም ጠይቀዋል፡፡ በሁለቱም ከተሞች ሕዝባዊ ስብሰባውን የመሩት ምክትል ሊቀመንበሩና ዋና ጸሐፊው እንደገለጹት በስብሰባው ላይ ከኢዜማ አባሎችና ደጋፊዎች ውጪ የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲ አባሎች በስብሰባው ላይ መገኘታቸውንና ጥያቄም አቅርበው ምላሽ እንደተሰጣቸው ገልጸዋል፡፡ ለሕዝባዊ ስብሰባ በሄዱባቸው ቦታዎች እንደታዘቡት ቅድሚያ ለሰላም ትኩረት ተሰጥቶ ሥራ መሠራት እንዳለበት፤ በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች የሚታየው ሥርዓት አልበኝነት ከምርጫው በፊት መቋጫ ሊበጅለት እንደሚገባ፤ ለሕዝቡም ከፍተኛ ስጋት እየሆነ እንደመጣም መገንዘባቸውን አሳውቀዋል፡፡

# የጥቅምት 2ቱ ሰላማዊ ሰልፍ የቀረበት ምክንያት በአስቸኳይ ለሕዝብ ይፋ እንዲደረግ የኢዜማ ሕዝብ ግንኙነት ጠየቀ

ጥቅምት 06 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ሕዝብ ግንኙነት ክፍል ጥቅምት 02 ቀን 2012 ዓ.ም ባወጣው መግለጫ በጋዜጠኛ እና የዴሞክራሲ ተሟጋች እስክንድር ነጋ አማካኝነት ተጠርቶ ሳይካሄድ የቀረው ሰላማዊ ሰልፍ መከልከሉ የመብት ጥሰት መሆኑን ገልፆ ይህን ዓይነት የመብት ጥሰት አጥብቆ እንደሚቃወም ገልጿል፡፡
የኢዜማ ሕዝብ ግንኙነት ክፍል በመግለጫው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰላማዊ ሰልፍ እና ሕዝባዊ ስብሰባ ማሳወቂያ ክፍል ለሰልፉ እውቅና የከለከለበት በቂ ምክንያት ካለው ቀደም ብሎ ለጠያቂዎቹና ለሕዝብ ማሳወቅ እንደነበረበት አመላክቷል፡፡ ሰልፉ የቀረበት ምክንያትም በአስቸኳይ ለሕዝብ ይፋ እንዲደረግ አጥብቀን እንጠይቃለን ብሏል፡፡
የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን በማኅበራዊ ገፁ ጥቅምት 01 ቀን 2012 ዓ.ም ባሰራጨው መልዕክት ሰላማዊ ሰልፍም ሆነ ስብሰባ በመስቀል አደባባይ የለም ብሏል፡፡ የሰልፉ አስተባባሪ እና የሕግ ባለሙያ የሆኑት ሔኖክ አክሊሉ የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ይህን መልዕክት በማኅበራዊ ገፁ ከማሰራጨቱ በፊትም ሆነ በኋላ ከሰልፉ አስተባባሪዎች ጋር ቀድሞ እንዳልተነጋገረ ለዜጎች መድረክ ገልፀዋል፡፡ የሕግ ባለሙያው እንደማንኛውም ግለሰብ ሰልፉ መከልከሉን ከማኅበራዊ ሚዲያው እንደሰሙ አስረድተዋል፡፡